# ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የተማሪ ምደባ ደንቦች

የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች የትምህርት የመከታተያ ዞን የሚወሰነው በትምህርት ቤት ቦርዱ ነው። ተማሪዎች ትምህርት የሚከታተሉት ትምህርት ቤት እነርሱ በሚኖሩበት በተከለለ ወይም ለእነርሱ በተመደበ አካባቢ ዞን ይሆናል።

ነገር ግን የተወሰኑ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በትምህርት ቤት አስተደደር(ዲቪዝን) የምደባ አማራጭ ለወላጆች /አሰዳጊዎች ይሰጣል። ይህም ከት/ቤት ከአቅም በላይ የሆነ ምደባ፣ የፕሮግራም ዝውውር፣ በወላጅ/አሳዳጊ ጥያቄ የአስተዳደር ዝውውር እና ምደባ፣ ለወንድም/እህት እና የወታደር ልጆች ምደባ ያካትታል።

የሚከተለት መመሪያዎች ሁለቱንም ፖሊሲዎች JC/JCD፤ የተማሪ ምደባ እና ይህን ደንብ ይገልፃል።

- ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በምድባቸው ባሉ ትምህርት ቤቶች ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎችን ይደግፋል በአፋጣኝ በማደግ ላይ ያለውን የተማሪዎች ቁጥር አማራጭ የመፈለግ አስፈላጊነት የሚረዳ ቢሆንም።
- ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በአንድ የትምህርት አካባቢ በአንድ የትምህርት ዓመት መረጋጋትን እና ቀጣይነትን መኖሩን ይደግፋል እንዲሁም በተቻለ መጠን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም በሙሉ እስከሚያጠናቅቁ።
- ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. አነስተኛ የክፍል መጠን እና የተወሰኑ የትምህርት ቤት ተማሪ የመቀበል ብቃትን ይደግፋል።
- ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በተቻለ መጠን ወንድም/እህት ተማሪዎችን በአንድ ላይ ማድረግን ይደግፋል።
- ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በወታደራዊ አገልግሎት የተሰማሩ የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ ይገነዘባል። በመሆኑም የሰራዊቱ አባላት ልጆችን የመቀበል ጥያቄ ያስተናግዳል።

ይህ ደንብ በተማሪዎች ምደባ መከተል የሚያስፈልገውን አሰራር ያስቀምጣል። በሁሉም ሁኔታዎች ሱፐር ኢንቴንደንቱ ወይም ተወካዮ የተማሪዎች ምደባን በሚመለከት የመጨረሻው የመወሰን ሥልጣን አለው።

ሁሉም ተማሪዎች እነርሱ በሚኖሩበት በተከለለ ወይም በተመደበ ዞን ባለ ትምህርት ቤት በቅድሚያ መመዝገብ አለባቸው ሌላ አማራጭ የተማሪ ምደባ ጥያቄ ከመቅረቡ ወይም ከመደረጉ በፊት።

## I. የተማሪ ምደባ አማራጮች

### A. በአቅም ምክንያት መልሶ ምደባ

በየዓመቱ በኤፕሪል 1 ሱፐር ኢንቴንደንቱ በቀጣዩ ዓመት በየትምህርት ቤቱ እና በየክፍል ደረጃ ሊኖር የሚችል የተማሪዎች ቁጥር ለህዝብ ያሳውቃል ። ሱፐር ኢንቴንደንቱ እና የትምህርት ቤቱ ቦርድ የቀረበውን የክፍል ደረጃ መጠን ገደብ እና በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚኖረውን የሆም ሩም ክፍሎች ብዛት በየክፍል ደረጃ በበጀት ዓመቱ በስፕሪንግ ወቅት ይመረምራል።

በፖሊሲ JC/JCD በአንዳንድ ሁኔታዎች ዝርዝር እንደተገለፀው የሱፐር ኢንቴንደንቱ በአንድ ት/ቤት ወይም በክፍል ደረጃ ባለው የመቀበል አቅም መሰረት የሚኖሩ የአንደኛ ደረጃ የተማሪዎች ቁጥር የክፍል መጠን ገደብ መወሰን ይችላል። የክፍል ደረጃ የመቀበል አቅም ከሞላ የሱፐር ኢንቴንደንቱ ወይም ተወካዮ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን ከሚኖሩበት በአቅራቢያቸው በሚገኙ የመቀበል አቅም ባላቸው ሌሎች ትምህርት ቤቶች እንዲደለደሉ ያደርጋል። የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የትራንስፖርት ሃብት እና አጠቃቀም በምደባው አሰራር ላይ ተጽእኖ የሚኖረው በመሆኑ “ከተማሪው መኖሪያ በቅርብ ያለ ትምህርት ቤት” በአጭር የመንዳት ርቀት(በማይል) ይወሰናል።

***መመሪያዎች***

- በአቅም ምክንያት ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ለተመደቡ ተማሪዎች ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል።
- በአንድ ትምህርት ቤት የተመደበ ተማሪ በአቅም ምክንያት ወደሌላ ትምህርት ቤት እንደገና አይመደብም። (ይህ መኖሪያ በመቀየር ምክንያት ትምህርት ቤት የቀየሩትን ልጆች እና በአስተዳደር ፈቃድ እስከ አመት መጨረሻ እንዲቆዩ የተፈቀደላቸውን ተማሪዎች አይመለከትም። እንዲሁም በዲቪዝኑ በሙሉ እንደገና ድልድል ምደባ እንዲደረግ በትምህርት ቤቱ ቦርድ የፀደቀውን አይመለከትም።)
- የክፍሉ መጠን የሞላ ቢሆንም እንኳ የትምህርት ቤቱ የወቅቱ ተማሪዎች የሆኑ ወንድምና እህት በዚያው ትምህርት ቤት እንዲመደቡ ይደረጋል ።
- ቦታ የሚገኝ ከሆነ በቀጣዪ የትምህርት ዓመት ሲጀመር ወደ መደበኛ የአካባቢያቸው ትምህርት ቤት ለመመለስ እንዲችሉ በቦታ መጣበብ ምክንያት በሌላ ት/ቤት የተመደቡ ተማሪዎች ስም የመልሶ ምደባ በተደረገበት ቅደም ተከተል መሰረት በተጠባባቂ ዝርዝር መዝገብ ውስጥ እንዲቆይ ይደረጋል ።
- ሌላ የተማሪ አማራጭ ምደባ ከመደረጉ በፊት ሁሉም ተማሪዎች በአካባቢያቸው ባለው ትምህርት ቤት በቅድሚያ መመዝገብ አላባቸው ።

***የመዋእለ ሕጻናት የሎተሪ አወጣጥ አሰራር***

***መደበኛ የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ ያላቸው ት/ቤቶች (TCS)***

በጁን 15 በአንድ ት/ቤት የመዋእለ ሕጻናት የመቀበል አቅም ያልሞላ ከሆነ ለሚቀጥለው ዓመት በትምህርት ቤቱ ለመግባት የተመዘገቡት ሁሉ እንዲገቡ ይደረጋል።

በት/ቤቱ የመዋእለ ሕጻናት ደረጃ ያለው አቅም ከሞላ ማማልከቻ ያስገቡት የመዋእለ ህጻናት ወላጅ/ አሳዳጊዎች በአንድ ላይ በመሰብሰብ ልጃቸው(ልጆቻቸው) በተማሪው መኖሪያ አቅራቢያ ባላ ሌላ ትምህርት ቤት እንዲመደቡ በራሳቸው ፈቃደኛ ስለመሆናቸው ይጠየቃሉ። ይህ ከሆነ ጥያቄያቸው ተቀባይነት የሚገኘው ሲሆን የትራንስፖርት አገልግሎትም ይሰጣል።

በጁላይ 1 ቀን ወይም ከዚያ በፊት ሁሉም አዲስ ማመልከቻ ያቀረቡ ተማሪዎችን ለመመደብ እጣ እንዲያውጡ ይደረጋል። እያንዳንዱ ተማሪ በእጣ መሰረት የቅደም ተከተል ምድብ ያገኛል ( በአንድ የክፍል ደረጃ ያሉ ወንድም እህት አንድ ዓይነት ደረጃ ይኖራቸዋል)። ተማሪዎች በአጎራባች ት/ቤት ክፍት ቦታው እንደየደረጃቸው ይመደባሉ ቦታው እስከሚሞላ ድረስ። ቀሪዎቹ ተማሪዎች በአቅም መሙላት ምክንያት መልሶ ድልድል መሰረት ወደሌላ ትምህርት ቤት ይመደባሉ።

ቦታ የሚገኝ ከሆነ በቀጣዪ የትምህርት ዓመት ሲጀመር ወደ መደበኛ የአካባቢያቸው ትምህርት ቤት ለመመለስ እንዲችሉ በቦታ መጣበብ ምክንያት በሌላ ት/ቤት የመልሶ ምደባ የተደለደሉ ተማሪዎች ስም በተሰጠው ቅደም ተከተል መሰረት በተጠባባቂ ዝርዝር መዝገብ ውስጥ እንዲቆዩ ይደረጋል ።

ሱፐር ኢንቴንደንቱ በሁሉም ህብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ወላጅ/ አሳዳጊዎችን በመድረስ ልጆቻቸውን ከጁን 15 በፊት እንዲያስመዘግቡ ለማበረታታት የማስተዋወቅ ፕሮግራም ስራ ያካሂዳል። ሱፐር ኢንቴንደንቱ ወላጅ/አሳዳጊዎችን ለማገዝ የሚያስችል የምዝገባ አሰራሩን የማሻሻል ስራ ያከናውናል፤

ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላት እንዲችሉ በአረፍት ጊዜ እና በጤና መዝገብ መረጃ ምክንያት የመጨረሻ የማስመዝገቢያ ቀናትን በማረዘም ጭምር።

**የተሻሻለ የጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር) ያላቸው ት/ቤቶች**

በጁን 1 በአንድ ት/ቤት የመዋእለ ሕጻናት የመቀበል አቅም ያልሞላ ከሆነ ለሚቀጥለው ዓመት በትምህርት ቤቱ ለመግባት የተመዘገቡት ሁሉ እንዲገቡ ይደረጋል።

በት/ቤቱ የመዋእለ ሕጻናት ደረጃ ያለው አቅም ከሞላ ማማልከቻ የሚያስገቡት የመዋእለ ህጻናት ወላጅ/አሳዳጊዎች በአንድ ላይ በመሰብሰብ ልጃቸው(ልጆቻቸው) በተማሪው መኖሪያ አቅራቢያ ባላ አቅም ባላው ሌላ ትምህርት ቤት እንዲመደቡ በራሳቸው ፈቃደኛ ስለመሆናቸው ይጠየቃሉ። ይህ ከሆነ ጥያቄያቸው ተቀባይነት የሚያገኙ ሲሆን የትራንስፖርት አገልግሎትም ይሰጣል።

በጁላይ 15 ቀን ወይም ከዚያ በፊት ሁሉም አዲስ ማመልከቻ ያቀረቡ ተማሪዎችን ለመመደብ እጣ እንዲያውጡ ይደረጋል። እያንዳንዱ ተማሪ በእጣ መሰረት የቅደም ተከተል ምድብ ያገኛል ( በአንድ የክፍል ደረጃ ያሉ ወንድም እህት አንድ ዓይነት ደረጃ ይኖራቸዋል)። ተማሪዎች ቦታው እስከሚሞላ ድረስ የተሻሻለ የጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር) ት/ቤት ባለው ክፍት ቦታው እንደየደረጃቸው ይመደባሉ ። ቀሪዎቹ ተማሪዎች በአቅም መሙላት ምክንያት መልሶ ድልድል መሰረት ወደሌላ ትምህርት ቤት ይመደባሉ።

ቦታ የሚገኝ ከሆነ በቀጣዩ የትምህርት ዓመት ሲጀመር ወደ መደበኛ የአካባቢያቸው ትምህርት ቤት ለመመለስ እንዲችሉ በቦታ መጣበብ ምክንያት በሌላ ት/ቤት የመልሶ ምደባ የተደለደሉ ተማሪዎች ስም በተሰጠው ቅደም ተከተል መሰረት በተጠባባቂ ዝርዝር መዝገብ ውስጥ እንዲቆዩ ይደረጋል ።

ሱፐር ኢንቴንደንቱ በሁሉም ህብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ወላጅ/ አሳዳጊዎችን በመድረስ ልጆቻቸውን ከጁን 1 በፊት እንዲያስመዘግቡ ለማበረታታት የማስተዋወቅ ፕሮግራም ስራ ያካሂዳል። ሱፐር ኢንቴንደንቱ ወላጅ/ አሳዳጊዎችን ለማገዝ የሚያስችል የምዝገባ አሰራሩን የማሻሻል ስራ ያከናውናል፤ ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላት እንዲችሉ በአረፍት ጊዜ እና በጤና መዝገብ መረጃ ምክንያት የመጨረሻ የማስመዝገቢያ ቀናትን በማረዘም ጭምር።

**B. የፕሮግራም ዝውውሮች**

በአንድ የተመረጡ ትምህርት ቤት የሚሰጠውን ፕሮግራም መሰረት በማድረግ የእነሱ ተማሪ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ውስጥ ባሉአ ት/ቤቶች እንዲዛወር ወላጆች መጠየቅ ይችላሉ። የተመረጡ የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ማለት በማውንት ቨርነን (Mount Vernon) እና በጆን አዳማስ (John Adams) የጥንድ ቋንቋ ፕሮግራም፣ በጀፍርሰን-ሂውስተን (Jefferson-Houston) የመዋእለ ህጻናት - 8 ፕሮግራም እና በሣሙኤል ተከር የተሻሻለ ጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር) ፕሮግራሞች ናቸው። እነዚህ ፕሮግራሞች በቅድሚያ በትምህርት ቤቱ ዞን ለሚኖሩ ተማሪዎች ክፍት ናቸው። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች በተጠየቀው የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ የሚኖር ከሆነ ከሌላ የትምህርት ቤት ዞን ዝውውር ይቀበላሉ ። የፕሮግራም ዝውውር ጥያቄዎች የሚፀድቁት በሱፐር ኢንቴንደንት ወይም በተወካዮ ነው።

እንደሌላው የዝውውር ዓይነት ሁሉ ሁሉም ተማሪዎች የዝውውር ጥያቄ ከማቅረባቸው በፊት በዞናቸው ባሉ ትምህርት ቤቶች በቅድሚያ መመዝገብ አለባቸው።

የፕሮግራም ዝውውሩ ተቀባይነት ካገኘ የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች በቀጣዩ የትምህርት አመት መጀመሪያ ላይ በመኖሪያ ዞናቸው ወደ አለው ትምህርት ቤት እንዲመለሱ መጠየቅ ይችላሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚያገኙት በተጠየቀው የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ የሚኖር ከሆነ ነው። በትምህርት ዓመቱ የሚቀርቡ ማናቸውም ጥያቄዎች እንደጥያቄው ሁኔታ አንድ በአንድ ይታያሉ።

### ከሌላ የትምህርት ቤት ዞን ወደ አንድ የትምህርት ቤት ፕሮግራም መግባት

ለተመረጠው የትምህርት ፕሮግራም ዝውውር የጠየቁት አመልካቾች በማንኛውም የትምህርት ደረጃ  ካለው ቦታ በላይ ከሆኑ  ከጁን 15 በኋላ ሁሉም አዲስ የፕሮግራም ዝውውር ጠያቂ ተማሪዎችን  ምደባ ለመወሰን እጣ እንዲያወጡ ይደረጋል።  (ሠንጠረዥ 1 ይመልከቱ፤ የምዝገባ  አሰራር  የመጨረሻ ቀናት።)

ለተመረጠው የትምህርት ፕሮግራም ዝውውር የጠየቁት ተማሪ አመልካቾች ቁጥር በማንኛውም የትምህርት ደረጃ  ካለው ቦታ በላይ ከሆኑ  ከጁላይ 1 በኋላ ሁሉም አዲስ የፕሮግራም ዝውውር ጠያቂ ተማሪዎችን  ምደባ ለመወሰን እጣ እንዲያወጡ ይደረጋል።  (ሠንጠረዥ 1 ይመልከቱ፤  የምዝገባ አሰራር  የመጨረሻ ቀናት።)

እያንዳንዱ ተማሪ በእጣ መሰረት የቅደም ተከተል ምድብ ያገኛል ( በአንድ የክፍል ደረጃ ያሉ ወንድም እህት አንድ ዓይነት ደረጃ ይኖራቸዋል)። ተማሪዎች በተመረጠው የትምህርት ፕሮግራም  ት/ቤት ክፍት ቦታው እስከሚሞላ ድረስ እንደአገኙት እጣ ደረጃቸው ይመደባሉ ። ቀሪዎች በዞናቸው ባሉ ትምህርት ቤቶች ትምህርት ይከታተላሉ። የተመረጡ የትምህርት ፕሮግራም ያላቸው  ሁሉም ት/ቤቶች በየዓመቱ የሎተሪ እድል ይኖራቸዋል ማለት አይደለም።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች ወንድምና እህት ተማሪዎች ወንድሞቻቸው በሚመሩበት ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይፈቀዳል ምንም እንኳ የትምህርት ቤቱ የክፍል መጠን የሞላ ቢሆንም።

### የጥምር ቋንቋ ፕሮግራም

የፕሮግራሙን የቅደም ተከተል ሂደትና ከትምህርት አሰጣጥ መሰፈርት ጋር ያለውን ትስስር በመመልከት ተማሪዎች የጥምር ቋንቋ ፕሮግራም መጀመር የሚገባቸው በህፃናት መዋያ ወይም አንደኛ ክፍል  ደረጃ ነው።  ማንኛውም ከክፍል 2-5 ባለ የክፍል ደረጃ በጥምር ቋንቋ ፕሮግራም ለመግባት የሚቀርብ የተማሪ ጥያቄ ተማሪውን በተገቢው የክፍል ደረጃ በፕሮግራሙ ሙሉ በሙሉ የመግባትና የመሳተፍ አቅም ለማረጋገጥ እንደየሁኔታው ይመረመራል።

በጥንድ ቋንቋ ፕሮግራም መሳተፍ የማይፈልጉ ተማሪዎች በዚያው ትምህርት ቤት ፕሮግራሙ  ካለ በመደበኛው ሥርዓተ ትምህርቱ ፕሮግራም መሳተፍ ይችላሉ።  ሆኖም ግን ትምህርት ቤቱ ያለው የጥንድ ቋንቋ ፕሮግራም ብቻ ከሆነ በመኖሪያ ቤቱ አቅራቢያ ወደሚገኘው በዚያ የክፍል ደረጃ ለመቀበል አቅም ባለው ት/ቤት የፕሮግራም ዝውውር ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች ወንድምና እህት ተማሪዎች ወንድሞቻቸው በሚመሩበት ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይፈቀዳል ምንም እንኳ የትምህርት ቤቱ የክፍል መጠን የሞላ ቢሆንም።

ወደ ትምህርት ቤት ፕሮግራሙ ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ ቤተሰቦች የትራንስፖርት  አገልግሎት ይሰጣል።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች በቀጣዩ የትምህርት አመት መጀመሪያ ላይ በመኖሪያ ዞናቸው ወደ አለው ትምህርት ቤት እንዲመለሱ መጠየቅ ይችላሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚያገኙት በተጠየቀው የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ የሚኖር ከሆነ ነው። በትምህርት ዓመቱ የሚቀርቡ ማናቸውም ጥያቄዎች እንደጥያቄው ሁኔታ አንድ በአንድ ይታያሉ።

***መዋእለ ህጻናት - 8 ትምህርት ቤቶች***

የመዋእለ ህፃናት - 8 ትምህርት ቤት በቅድሚያ በትምህርት ቤት ዞኑ ለሚኖሩ ተማሪዎች ክፍት ይሆናል። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች በተጠየቀው የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ የሚኖር ከሆነ ብቻ ከሌላ የትምህርት ቤት ዞን ዝውውር ይቀበላሉ ።በትምህርት ቤት ዞናቸው በተመደቡ የመዋእለ ህፃናት - 8 ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ለመግባት መምረጥ ይችላሉ ።

የመዋእለ ህፃናት - 8 ትምህርት ቤት የሚከታተሉ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ከስድስተኛ ክፍል ጀምሮ ከት/ቤቱ መውጣት ይችላሉ። ሆኖም ከዚያ በፊት አይቻልም። የመዋእለ ህፃናት - 8 ትምህርት ቤቶች ያሉት የመዋእለ ህፃናት - 5 ፕሮግራሞች በመደበኛ ት/ቤቶች ከሚሰጡት ፕሮግራሞች ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። በዞናቸው የሚገኙ መደበኛ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለመግባት እነርሱ ካልመረጡ በስተቀር ተማሪዎች የመካከለኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በዚያው ትምህርት ቤት እንዲቀጥሉ ይደረጋል ።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች ወንድምና እህት ተማሪዎች ወንድሞቻቸው በሚመሩበት ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይፈቀዳል ምንም እንኳ የትምህርት ቤቱ የክፍል መጠን የሞላ ቢሆንም።

ወደ ትምህርት ቤት ፕሮግራሙ ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ ቤተሰቦች የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች በቀጣዪ የትምህርት አመት መጀመሪያ ላይ በመኖሪያ ዞናቸው ወደ አለው ትምህርት ቤት እንዲመለሱ መጠየቅ ይችላሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚያገኙት በተጠየቀው የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ የሚኖር ከሆነ ነው። በትምህርት ዓመቱ የሚቀርቡ ማናቸውም ጥያቄዎች እንደጥያቄው ሁኔታ አንድ በአንድ ይታያሉ።

**የተሻሻለ የጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር) ፕሮግራም**

የተሻሻለ የጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር) ፕሮግራም ተማሪዎች የሚከታተሉት የትምህርት ቀናት ቁጥር በመደበኛ ትምህርት ቤት ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን ሰላሳ ተጨማሪ የትምህርት ቀናት የመከታተል አማራጭ አላቸው። ተጨማሪዎቹ ቀናት በዓመቱ በመላ የተሰራጩ በመሆኑ በክፍለ ጊዜዎች(ኢንተር ሲሽን) መሃል ባለው ጊዜ ተማሪዎች በተራዘመ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የመሳተፍ እድል ይኖራቸዋል ።

የሣሙኤል ተከር ( Samuel W. Tucker) አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተሻሻለ የጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር) ፕሮግራም ይከተላል። ይህ ፕሮግራም በቅድሚያ በትምህርት ቤቱ ዞን ለሚኖሩ ተማሪዎች ክፍት ነው። በዚህ ትምህርት ቤት በተጠየቀው የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ የሚኖር ከሆነ ብቻ ከሌላ የትምህርት ቤት ዞን ዝውውር ይቀበላል ።

በትምህርት ቤት ዞኑ ኖሪ የሆኑ የተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች የተሻሻለውን የጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር) ፕሮግራም መከታተል የማይፈልጉ ከሆነ በተማሪው መኖሪያ አቅራቢያ ወደአለው በዚያ የክፍል ደረጃ የመቀበል አቅም ባለው ትምህርት ቤት የፕሮግራም ዝውውር መጠየቅ ይችላሉ።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች ወንድምና እህት ተማሪዎች ወንድሞቻቸው በሚመሩበት ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይፈቀዳል ምንም እንኳ የትምህርት ቤቱ የክፍል መጠን የሞላ ቢሆንም።

ወደ ትምህርት ቤት ፕሮግራሙ ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ ቤተሰቦች የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች በቀጣዪ የትምህርት አመት መጀመሪያ ላይ በመኖሪያ ዞናቸው ወደ አለው ትምህርት ቤት እንዲመለሱ መጠየቅ ይችላሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚያገኙት በተጠየቀው የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ የሚኖር ከሆነ ነው። በትምህርት ዓመቱ የሚቀርቡ ማናቸውም ጥያቄዎች እንደጥያቄው ሁኔታ አንድ በአንድ ይታያሉ።

**C. አስተዳደራዊ ዝውውር**

የተማሪውን ልዮ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ወላጆች ለልጃቸው(ጆቻቸው) አስተዳደራዊ ዝውውር መጠየቅ ይቻላሉ። አስተዳደራዊ ዝውውር ማለት አንድ ተማሪ በደህንነት፣ በጤና ወይም ጊዚያዊ ወይም በትምህርት ዓመቱ መሃል የመኖሪያ ቤት መቀየር ምክንያት በወላጅ/አሳዳጊ ጥያቄ እና በአስተዳደር ሃላፊ በተሰጠ አስተዳደራዊ ፍቃድ ተማሪው ተጠቃሚ ለማድረግ የትምህርት ቤት አካባቢ እንዲቀየር ከአንድ ት/ቤት ወደሌላ እንዲዛወር ማድረግ ነው ። የአስተዳደራዊ ዝውውር ጥያቄዎች የሚፀድቁት በሱፐር ኢንቴንደንት ወይም በተወካዮ ነው።

**በትምህርት ቤት ክልሉ(ዲቭዝኑ) የውስጥ ዝውውር**

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ትምህርት ቤት የሚከታተል ተማሪ እና ቤተሰቡ የትምህርት ዘመኑ ከተጀመረ በኋላ ወደሌላ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የትምህርት ቤት ዞን ከቀየሩ አሁን እርሱ/እርሷ ባለበት/ባለችበት ትምህርት ቤት ለዚያ የትምህርት ዓመት በአስተዳደራዊ ዝውውር ፈቃድ ብቻ የመቆየት ምርጫ ይኖረቸዋል። ተማሪው በዚያ ትምህርት ቤት ለመቆየት ከመረጠ የትራንስፖርት አገልግሎት አያገኝም።

**ወደ ሌላ የትምህርት ክልሎች (ዲቪዝኖች) መቀየር**

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ትምህርት ቤት የሚከታተል ተማሪ እና ቤተሰብ የትምህርት ዘመኑ ከተጀመረ በኋላ በአራተኛው ኮርተር ወደ ሌላ የትምህርት ክልል (ዲቪዝን) ከቀየሩ አሁን እርሱ/እርሷ ባለበት/ባለችበት ትምህርት ቤት የዚያ ቀሪ የትምህርት ዓመት ለመጨረስ በአስተዳደራዊ ዝውውር ፈቃድ ብቻ የመቆየት ምርጫ ይኖረቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ትምህርት ቤት የሚከታተል የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ እና ቤተሰብ ሁለተኛው የትምህርት ኮርተር ከተጀመረ በኋላ ወደሌላ ወደ ሌላ የትምህርት ክልል (ዲቪዝን) ከቀየሩ አሁን እርሱ/እርሷ ባለበት/ባለችበት ትምህርት ቤት የዚያ ቀሪ የትምህርት ዓመት በአስተዳደራዊ ዝውውር ፈቃድ ብቻ የመቆየት ምርጫ ይኖረቸዋል። ይህ በተለይ የሚሰጥ ፈቃድ በተማሪው መልካም ሁኔታ፤ ጥሩ ባህሪ ማሳየት፣ በትምህርት መከታተል፣ እና የአካዳሚ ሁኔታ ላይ ይመሰረታል። የትራንስፖርት አገልግሎት አይሰጥም።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች ወንድምና እህት ተማሪዎች ወንድሞቻቸው በሚመሩበት ትምህርት ቤት እንዲከታተሉ ይፈቀዳል ምንም እንኳ የትምህርት ቤቱ የክፍል መጠን የሞላ ቢሆንም።

በወላጅ/ አሳዳጊ ጠየቂነት ለሚደረግ አስተዳደራዊ ዝውውሮች የትራንስፖርት አገልግሎት አይሰጥም። በጣም በተወሰነ ሁኔታ በሱፐር ኢንቴንደንት ወይም በተወካዩ በደንብ ከተመረመረ በኋላ የትራንስፖርት አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል።

እንደሌላው የዝውውር ዓይነት ሁሉ ሁሉም ተማሪዎች የዝውውር ጥያቄ ከማቅረባቸው በፊት በዞናቸው ባሉ ትምህርት ቤቶች በቅድሚያ መመዝገብ አለባቸው።

አንዴ ከፀደቀ በኋላ አስተዳደራዊ ዝውውሩ ለዓመታት በስራ ላይ በትምህርት ቤቱ እንዲቆይ ይደረጋል የሚከተሉት እስከተሟላ ድረስ፤

- በፖሊሲ JED መሰረት ልጁ ትምህርቱን በጥሩ የሚከታተልና በሰዓቱ የሚገኝ ከሆነ ፣
- ልጁ በትምህርት ቤት መልካም ተገቢ ባህሪ የሚያሳይ ከሆነ።

ርእሰ መምህሩ፣ ሱፐር ኢንቴንደቱ ወይም የእርሱ ተወካይ ከእነዚህ ሁለት መስፈርቶች መካከል አንደኛውን በተመለከተ በቂ አሳሳቢ ሁኔታዎች አለ ብለው ካመኑ እንዲሁም ተማሪው በዞኑ ባለ ትምህርት ቤት እንዲመለስ ከወሰኑ ወላጅ በዚያው ዓመት ሜይ 1 እንዲያውቀው ይደረጋል።

አዲስ የዝውውር ጥያቄ የሚታየው በዚያ ትምህርት ቤት የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ ሲኖር ነው።

አስተዳደራዊ የዝውውር ጥያቄ መቅረብ የሚኖርበት ለተማሪዎች አገልግሎት የአማራጭ ፕሮግራም እና ፍትሃዊነት ዲፓርትሜንት (Department of Student Services, Alternative Programs and Equity) ነው። የመጠያቂያው ቅፅ ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ድረገፅ ወይም ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ዋና ጽህፈት ቤት ማግኘት ይቻላል።

የፕሮግራም ዝውውር ያገኙ ተማሪዎች በቀጣዩ የትምህርት አመት መጀመሪያ ላይ በመኖሪያ ዞናቸው ወደ አለው ትምህርት ቤት እንዲመለሱ መጠየቅ ይችላሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚያገኙት በተጠየቀው የክፍል ደረጃ ክፍት ቦታ የሚኖር ከሆነ ነው። በትምህርት ዓመቱ የሚቀርቡ ማናቸውም ጥያቄዎች እንደጥያቄው ሁኔታ አንድ በአንድ ይታያሉ።

**D. ልዩ ሁኔታ**

**የሰራዊቱ አባላት ልጆች ምደባ**

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በወታደራዊ አገልግሎት የተሰማሩ የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ ይገነዘባል። በመሆኑም የሰራዊቱ አባላት ልጆችን የመቀበል ስራ በ Interstate Compact on Educational Opportunity for Military Children (ቨርጂኒያ ህግ § 22.1-360) በተገለፀው መሰረት ያከናውናል። ይህም የሚያካትተው ምንም እንኳ የክፍሉ መጠን የሞላ ቢሆንም ቀደም ሲል ምድባቸውን ከመቀየራቸው በፊት ሲከታተሉበት በነበረው ትምህርት ቤት መመለስ ወይም የሰራዊቱ ቤተሰብ በሚኖሩበት አካባቢ በሚገኝ ትምህርት ቤት መመደብ ይጨምራል።

የሰራዊቱ አባላት ልጆችን የትምህርት እድል የስቴቶች ስምምነት እና ፖሊሲ( JHCB) መሰረት የሰራዊቱ አባላት ልጆችን በትምህርት ቤት ከተመዘገቡ በኋላ ተፈላጊ ክትባቶችን ለማሟላት 30 ቀናት ይኖራቸዋል። ተካታታይነት ያላቸው ክትባቶች እና የመጀመሪያ ክትባቶች 30 ቀናት ውስጥ በግድ መቅረብ አለባቸው።

**የወንድም/እህት(ሲብሊንግ) ህግ**

የክፍሉ መጠን የሞላ ቢሆንም እንኳ የትምህርት ቤቱ የወቅቱ ተማሪዎች የሆኑ ወንድምና እህት በዚያው ትምህርት ቤት እንዲመደቡ ይደረጋል ።

**የከተማ አቀፍ ፕሮግራም የአካል ጉዳት ላላቸው ተማሪዎች**

በአይ.ኢ.ፒ. (IEP) ቡድን ምደባ መሰረት በከተማአቀፍ ልዩ የትምህርት ፕሮግራም የሚመደቡ ተማሪዎችን ይህ ፖሊሲ አይመለከትም። እነዚህም ፕሮግራሞች የስሜት ጉዳት(ኢሞሽናል ዲሴብሊቲ-ED)፣ የአእምሮ ጉዳት (ኢንተሌክችዋል ዲሴብሊቲ- ID)፣ በርካታ ጉዳት(መልቲፐል ዲሴብሊቲ- MD)፣እና ኦቲዝም ያላቸው ተማሪዎች ፕሮግራሞች እና ቅድመ መደበኛ ትምህርት ልዮ ትምህርት (ECSE)ያጠቃልላል።

## II.ተጨማሪ መግለጫ

***የቃላት መፍቻ***

***የዞን ትምህርት ቤት፤*** በመኖሪያ አድራሻው መሰረት ተማሪው ትምህርት እንዲከታታል የተመደበበት ትምህርት ቤት እና በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ትምህርት ቤት ቦርድ የፀደቀ የትምህርት ቤት ዞን ድንበር።

***አሁን ያሉበት ትምህርት ቤት፤*** በሌላ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ተማሪው አሁን ትምህርት የሚከታተልበት ት/ቤት ።

***የአቅም ስፋት መጠን መልሶ ምደባ፤*** በትምህርት ቤት ዞን ድንበር ውስጥ ባለ ትምህርት ቤት አንድ ክፍል ውስጥ የአቅም መሙላት ምክንያት የሚደረግ እንደገና ምደባ። በአቅም ምክንያት ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ለተመደቡ ተማሪዎች ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል።

***የፕሮግራም ዝውውሮች፤*** ወደ ተመረጡ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ( የጥንድ ቋንቋ ፕሮግራም ፣ የመዋእለ ህጻናት - 8 ፕሮግራም እና የተሻሻለ ጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር) ፕሮግራም የመግባት እና የመውጣት ዝውውር ። ወደ ተመረጡ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ ቤተሰቦች የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል።

***አስተዳደራዊ ዝውውር፤*** አንድ ተማሪ በደህንነት፣ ጤና ወይም ጊዚያዊ ወይም በትምህርት ዓመቱ መሃል የመኖሪያ ቤት መቀየር ምክንያት በወላጅ/አሳዳጊ ጥያቄ እና በአስተዳደር ሃላፊ በተሰጠ አስተዳደራዊ ፍቃድ ተማሪው ተጠቃሚ ለማድረግ የትምህርት ቤት አካባቢ እንዲቀየር ከአንድ ት/ቤት ወደሌላ እንዲዛወር ማድረግ። የአስተዳደራዊ ዝውውር ጥያቄዎች የሚፀድቁት በሱፐር ኢንቴንደንት ወይም በተወካዮ ነው። በወላጅ/ አሳዳጊ ጠየቂነት ለሚደረግ አስተዳደራዊ ዝውውሮች የትራንስፖርት አገልግሎት አይሰጥም። የመጠለያ መኖሪያ ለሌለው ተማሪ በሱፐር ኢንቴንደንት በልዮ አስተያየት ሊደረግ ይችላል።

***ሎተሪ፤*** አዲስ የሚመዘገቡ ተማሪዎች በክፍል ወይም በትምህርት ቤት ደረጃ ካለው ክፍት ቦታ መጠን በላይ ሲሆን የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ የሚከተለው የአሰራር ሂደት። የምደባ ቅደም ተከተል ለመወሰን እያንዳንዱ ተማሪ እጣ ቁጥር ይመደባል።

***በተማሪው መኖሪያ አቅራቢያ ያለ ትምህርት ቤት፤*** ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ የትራንስፖርት ሃብት መጠንና አጠቃቀም በአመዳደብ አሰራር ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር በመሆኑ ምክንያት የሚሰነው በአጭር የመንዳት ርቀት(ማይል) ነው።

**ሠንጠረዥ 1፡ የምዝገባ አሰራር የመጨረሻ ቀን**

| **የምዝገባ አሰራር** (የሱፐር ኢንቴንደንት ለቀጠዪ የትምህርት ዓመት (SY) የምዝገባ ፕሮጀክት በኤፕሪል 1) | **ወላጅ/ አሳዳጊ ማመልከቻ የመጨረሻ ቀን በ፤** | **ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሎተሪ የሚካሄደው በ፤** | **ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ማስታወቂያ /ውጤት ለወላጅ/አሳዳጊ በ፤** |
|---|---|---|---|
| **ማስታወቂያ የአስተዳደራዊ ዝውውር የሚሰረዝበት** (ለቀጣዪ የትምህርት ዓመት በትምህርት ላይ ባለመገኘት/ በባህሪ ደንብ መጣስ ምክንያት ) | | | ሜይ 1 |
| **የተሻሻለ የጊዜ ሰሌዳ (ካላንደር) ት/ቤት (MCS) ፕሮግራም ሎተሪ** (አስፈላጊ ከሆነ ) | ጁን 1 | ጁን 15 | ጁላይ 1 |
| **ሌላ የተመረጡ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ሎተሪዎች** (አስፈላጊ ከሆነ) | ጁን 15 | ጁላይ 1 | ኦገስት 1 |
| **የተሻሻለ ካላንደር የመዋእለ ህፃናት ሎተሪ** (በጁን 1 የሚገለፅ አስፈላጊ ከሆነ) | ጉዳዩ አይመለከተውም | ጁን 15 | ጁላይ 1 |
| **የመደበኛ ካላንደር የመዋእለ ህፃናት ሎተሪ** (በጁን 15 የሚገለፅ አስፈላጊ ከሆነ) | ጉዳዩ አይመለከተውም | ጁላይ 1 | ጁላይ 15 |

**ሠንጠረዥ 2፡ የተማሪው ምደባ እና ትራንስፖርት**

| **ምድብ ዓይነት** | **ትራንስፖርት ምደባ ለተማሪውና ለወንድምና እህት** |
|---|---|
| **ከአቅም በላይ መልሶ ምደባ** | አዋ |
| **የፕሮግራም ዝውውሮች** | አዋ |
| **አስተዳደራዊ ዝውውር** | አይ |
| **አስተዳደራዊ ዝውውር መጠለያ ለሌላቸው ተማሪዎች** | አዋ |
| **የከተማ አቀፍ ፕሮግራም የአካል ጉዳት ላላቸው ተማሪዎች** | አዋ |

| | |
|---|---|
| የተሻሻለው፤ | ሜይ 8፣ 2013 |
| የተሻሻለው፤ | ሜይ 28፣ 2015 |
| የተሻሻለው፤ | ሴፕቴምበር 11፣ 2015 |
| የተሻሻለው፤ | ሜይ 19፣ 2016 |

| | | |
|---|---|---|
| የቃላት መፍቻ፤ | IHB | የክፍል አቅም |
| | IHB-R | ከክፍል አቅም ጋር የተገናኙ ደንቦች |
| | JC/JCD | የተማሪ ምደባ |
| | JCE | ዞን መልሶ የማካለል አፈፃፀም |
| | JCE-R | ዞን መልሶ የማካለል አፈፃፀም ደንቦች |
| | JED | የተማሪ መቅረት/ፈቃድ /ማባረር |
| | JHCB | የተማሪ ክትባቶች |